የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

**Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority**

# የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሳሪያዎች አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥር መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 01/2010

2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

1. <u>መግቢያ</u>

የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥር መመሪያ 01/2006 እና መመሪያውን ለማሻሻል የወጣውን መመሪያ 01/2009ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ መመሪያቹን ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽለዋል።

2. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥር መመሪያ 01/2006 እና 2009ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 01/2010 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. <u>ማሻሻያ 01/2006</u>

የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥር መመሪያ 01/2006 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. የመመሪያው አንቀጽ 2 የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ ተጨምሮበታል።

"(10)" "መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት" ማለት በንግድ ስራ ያልተሰማራ እና በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰራ በሚመለከተው አካል ሕጋዊ ፈቃድ የተሰጠው ሀገር በቀል ወይም የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ነው።"

4. <u>ማሻሻያ 01/2009</u>

የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ለማሻሻል የወጣው መመሪያ 01/2009 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. የመመሪያው አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 4 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል።

"18 ንኡስ አንቀጽ 4" ማንኛውም አስመጪ ድርጅት የእንስሳት መድኃኒት ወይም የሕክምና መሳሪያ መሸጥ የሚችለው የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላለው ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ወይም አስመጪው ራሱ ያስመጣውን የእንስሳት መድኃኒት ወይም የሕክምና መሳሪያ በጅምላ ለሚገዙ መንግስታዊ ተቋማት ወይም መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ብቻ ነው።



Ministry of Live Stock & Fisheries Drug & Animal Feed Administration & Control Authority

2. የመመሪያው አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 10 እና አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 11 ሙሉ በሙሉ ከመመሪያው ተሰርዘዋል፡፡

3. የመመሪያው አንቀጽ 18 የሚከተሉት ንኡስ አናቅጽት ተጨምረውበታል፡፡

"18 ንኡስ አንቀጽ 13" ማንኛውም አምራች ወይም አስመጪ ድርጅት የጅምላ አከፋፋይነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው ካመረተው ወይም ካስመጣው የእንስሳት መድኃኒት ወይም የሕክምና መሳሪያ ውጪ በሌላ በማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይም የሕክምና መሳሪያ ጅምላ ንግድ ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

"18 ንኡስ አንቀጽ 14" የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 13 አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጅምላ የእንስሳት መድኃኒት ወይም የሕክምና መሳሪያ ግዥ መፈጸም የሚችለው ከባለስልጣን መ/ቤቱ ልዩ ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

5. ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ ማሻሻያ መመሪያ ከጥር 3 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ጥር 3 ቀን 2010 ዓ.ም.

ጠርዙ ዳያ ደጋጋ (ዶ/ር)

የአንስሳት መድኃኒት መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

ጠርዙ ዳያ ደጋጋ (ዶ/ር)
የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና
ቁጥጥር ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር